የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ኤጀንሲ

The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Charities and societies Agency

ቁጥር 03/CHSA-64.209
Ref. No.

ቀን 11 የካቲት 2007
Date

ለ አማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት አስተዳደርና ፀጥታ ጉዳይ ቢሮ
ለ አማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ
ባህር ዳር
ለ ትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፍትህ ቢሮ
ለ ትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ
መቐለ
ለ ደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፍትህ ቢሮ
ለ ደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ
ሐዋሳ
ለ አፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት አስተዳደርና ፀጥታ ጉዳይ ቢሮ
ለ አፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ
ሰመራ
ለ ሶማሌ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፀጥታና አስተዳደር ቢሮ
ለ ሶማሌ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ
ጅግጅጋ
ለ ጋምቤላ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፍትህ ቢሮ
ለ ጋምቤላ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ
ጋምቤላ
ለ ቤንሻንጉል ጉምዝ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፍትሕ ቢሮ
ለ ቤንሻንጉል ጉምዝ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ
አሶሳ
ለ ሐረሪ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፍትህና ፀጥታ አስተዳደር ቢሮ
ለ ሐረሪ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ
ሐረር
ለ ድሬዳዋ አስተዳደር ፍትህና ፀጥታ አስተዳደር ቢሮ
ለ ድሬዳዋ አስተዳደር ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ
ድሬዳዋ
ለ አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ
ለ ኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ
አዲስ አበባ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ኤጀንሲ
The Federal Democratic Republic of Ethiopia Charities and Societies Agency

ጉዳዩ:- በመመሪያ ቁጥር 02/2003 ለሁለተኛ ጊዜ ተሻሽለው መካተት ያለባቸው ጉዳዮች ማሳወቅን ይመለከታል።

በጉዳዩ ላይ እንደተጠቀሰው የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት የዓላማ ማስፈፀሚያና አስተዳደራዊ ወጪዎችን ለመወሰን በወጣው መመሪያ ቁጥር 02/2003 ላይ በታተመው መመሪያ ከአባሪው ቀጥሎ ከገጽ 1-10

ስልክ Tel. +0111110340 | ቴሌ ፋክስ FAX +0111567825 | ፖ.ሣ.ቁ P.O.Box 14340 | ድረ-ገጽ Web-sit www.chsa.gov.et. | አዲስ አበባ - ኢትዮጵያ Addis Ababa - Ethiopia

አካትቶ ማቅረቡ ይታወቃል፣ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ለሁለተኛ ጊዜ የተደረጉ ማሻሻያዎችን የያዘ 7 ገጽ ከዚህ እንደሚከተለው አባሪ አድርገን የላክን መሆኑን እያሳወቅን ማሻሻያው ከቀን 10/06/2007 ዓ.ም ጀምሮ ሥራ መዋሉን እየገለጽን ማሻሻያዎቹን እንደሚከተለው አቅርበናል፡፡

1. ***ለበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት የዓላማ ማስፈፀሚያ ወጪዎች ዝርዝር***

1.1 የኤች.አይ.ቪ. ኤድስ ቫይረስ በደማቸው ውስጥ የሚገኙ ወገኖችን ተጠቃሚነት ለማጎልበት የዓላማ ማስፈፀሚያ ወጪ ሥር የሚካተቱ ተጨማሪ የወጪ ርእሶች፡-

1.1.1 እንክብካቤና ድጋፍን የሚሰጡ ሞግዚት ተንከባካቢዎች የደመወዝ ወጪ፣

1.1.2 ቤት ለቤት እየተዘዋወሩ ድጋፍን የሚሰጡ ተቀጣሪ ሠራተኞች የደመወዝ ወጪ፣

1.1.3 ወላጆቻቸውን በኤች.አይ.ቪ. ኤድስ ያጡ ህፃናትን በማሳደጊያ ማእከል ለህፃናቱ ጤናማ አካላዊና ስነ-ልቦናዊ እድገት ድጋፍና ክትትልን ያደርጉ ዘንድ የመደቧቸው ቋሚ ተቀጣሪ የጤና ባለሙያዎች የደመወዝ ወጪ፣

1.1.4 በማንኛውም የበጎ አድራጎት ድርጅትም ሆነ ማህበር ውስጥ የኤች.አይ.ቪ. ኤድስ በደሙ ያለበት ተቀጣሪ ሆኖ ሲሰራ ለግለሰቡ የሚከፈል የደመወዝ ወጪ፡፡

1.2 የአካል ጉዳተኛ ወገኖችን ተጠቃሚነት ለማጐልበት የዓላማ ማስፈፀሚያ ወጪ አውድ ሥር የሚካተቱ ተጨማሪ የወጪ ርእሶች፡-

1.2.1 ለአካል ጉዳተኞች በተለየ ሁኔታ የተሰራ ተሽከርካሪ ግዥ ሲፈፅም የተሽከርካሪው ግዥ ወጪ እና ተሽከርካሪው አገልግሎት ሲሰጥ የሚያስፈልጉት የነዳጅ፣ የተሽከርካሪው ማለሳለሻ ቅባቶችና የጥገና ወጪዎች፣

1.2.2 ለአካል ጉዳተኞች እንክብካቤና ድጋፍ ይሰጡ ዘንድ የመደቧቸው ረዳቶች፣ ቋሚ ተቀጣሪ ከሆኑ የሠራተኞቹ የደመወዝ ወጪ፣

1.2.3 ለአካል ጉዳተኛ እንክብካቤና ድጋፍን የሚሰጡ ሞግዚቶች ተንከባካቢዎች የደመወዝ ወጪ፣

1.2.4 ቤት ለቤት እየተዘዋወሩ እንክብካቤና ድጋፍ የሚሰጡ ቋሚ ተቀጣሪ ሠራተኞች የደመወዝ ወጪ፣

1.2.5 በአካል ጉዳተኞች ዙሪያ ብቻ ታልሞ ለሚቋቋም ማሰልጠኛ ተቋም የሚወጣ ወጪ፣

1.2.6 በቅጥር ግቢ ውስጥ ለአካል ጉዳተኛ ወገኖች ተደራሽነትና ምቹነት ሲባል የሚገነባ የውስጥ ለውስጥ መንገድ ግንባታ ወጪ፣

1.2.7 በማንኛውም የበጎ አድራጎት ድርጅትም ሆነ ማህበር ውስጥ የአካል ጉዳት ያለበት ተቀጣሪ ሆኖ ሲሰራ ለግለሰቡ የሚከፈል የደመወዝ ወጪ፣

1.3 የንፁህ መጠጥ ውሃ አቅርቦትን ከማሻሻል እና ከንፅህና አጠቃቀም አንፃር የዓላማ ማስፈፀሚያ ወጪ አወድ ሥር የሚካተቱ ተጨማሪ የወጪ ርእሶች፡-

1.3.1 የንፁህ መጠጥ ውሃን ለማጎልበት ይረዳው ዘንድ የሚፈፅማቸው የጉድጓድ ውሃ መቆፈሪያ መሳሪያ ተሽከርካሪ /ማሽን-ሪግ/ ግዥና ተሽከርካሪው አገልግሎትን ሲሰጥ የሚያስፈልጉት የነዳጅ፣ የተሽከርካሪ ማለስለሻ ቅባቶችና የጥገና ወጪዎች እንዲሁም በዚሁ ተሽከርካሪ ላይ ተቀጥሮ የሚሰራው ተሽከርካሪ ሾፌር /ኦኘሬተር/ የደመወዝ ወጪ፣

1.3.2 የንፁህ መጠጥ ውሃን ለማዳረስ የተገነቡ እንደ ቦኖ ውሃ ያሉ የመጠጥ ውሃ ማከፋፈያዎችን ይቆጣጠሩና ይጠብቁ ዘንድ የቀጠሯቸው ወይም የመደቧቸው ሠራተኞች ደመወዝ ወጪ፣